9ኛ ዓመት ቁጥር 12
9th Year No. 12

ባህር ዳር ሚያዝያ 12 1996 ዓ/ም
Bahir Dar, 20th April, 2004

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት
ዝክረ ህግ
ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር 3.50
Unit price 3.50

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 99/1996 ዓ.ም.
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የውሃ ሃብት ልማት ቢሮ ማቋቋሚያና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ

አዋጅ ቁጥር 99/1996 ዓ.ም.

በአማራ ብሔራዊ ክልል መንግስት የውሃ ሃብት ልማት ቢሮን ለማቋቋምና ሥልጣንና ተግባራትን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

የብሔራዊ ክልሉ የውሃ ሃብት በሚገባ ለምቶ ለኢኮኖሚው ጉልህ አስተዋጽኦ ማበርከት የሚጠበቅበት ቢሆንም በክልሉ ውስጥ በውሃው ዘርፍ ተሰማርተው የተለያዩ ተግባራትን የሚያከናውኑ መንግስታዊም ሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ አካላትና ድርጅቶች የአቅም ማነስ የሚታይባቸው በመሆኑ የተናጠል ጥረቶቻቸውን ማስተባበርና የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በክልሉ ውስጥ የሚገኙት የውሃ ሃብት አልሚና ተቆጣጣሪ መሥሪያ ቤቶች ኃላፊነታቸውን በብቃት ለመወጣት ያስችላቸው ዘንድ እስካሁን የነበራቸውን አደረጃጀት በማሻሻል የዘርፉ አስተዳደር ውጤታማና ዘላቂነት ያለው ሆኖ እንዲፈፀምና ለክልሉ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ እድገት የላቀ አስተዋጽኦ እንዲኖረው ማድረግ በማስፈለጉ፤

Content

Proclamation No. 99/2004
The Amhara National Regional State Water Resource Development Bureau Establishment and Determination of its Powers and Duties Proclamation

Proclamation No. 99/2004

A Proclamation Issued for the Establishment of the Amhara National Regional State Water Resource Development Bureau and Determination of its Powers and Duties

WHEREAS, though water resource of the National Region is expected to get developed and provide major contributions for the economy, capacity inadequacy is observed with those governmental as well as non-governmental bodies and organizations involved in undertaking various activities in the water sector in the Region, and it is thus found necessary to co-ordinate the independent efforts of same to attain better result;

WHEREAS, with a view to enabling water resource developing and supervising offices to discharge their responsibilities efficiently, it is necessary to improve their hitherto organizational structure and thereby cause the administration of the sector to be carried out being effective as well as sustainable and to make it have highest benefits to the soci- economic development of the Region;

በአካባቢያችን በሚከሰተው ተደጋጋሚ የዝናብ እጥረት ማቢያ በሰው፣ በእንስሣትና በአጠቃላይም በተፈጥሮ ላይ እየደረሰ ያለውን የድርቅ አደጋ ለመከላከል ብቻ ሣይሆን በቤተሰብ ደረጃ የምግብ ዋስትናን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማረጋገጥና ድህነትን ለማጥፋት እንዲቻል ሃብቱ ውሱንና ውድ ከመሆኑ የተነሣ ተገቢው ጥበቃና እንክብካቤ ተደርጎለትና በቁጠባ ለምቶ አገልግሎት ላይ እንዲውልና ተራፊውም ሣይበከል ለትውልድ እንዲተላለፍ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ዘርፉን በብቃት ማደራጀት እንደሚገባ የታመነበት በመሆኑ፣

በክልሉ ውስጥ የተቀናጀ የውሃ ሃብት አስተዳደር ስልት ተቀይሶ ተግባራዊ የሚደረግበትንና ሃብቱም ወጥነት ባለው መንገድ የሚመራበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠርና ለዚህም ይረዳ ዘንድ ሥራውን የሚያስተባብር ተጠሪና ተቆጣጣሪ አካል በሕግ መሰየም ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ ሥር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የውሃ ሃብት ልማት ቢሮ ማቋቋሚያና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 99/1996 ዓ.ም." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ:-

1. "የውሃ ሃብት" ማለት የገፀ-ምድርና የከርሰ-ምድር ውሃ እንዲሁም በአየር ውስጥ የሚገኝ እርጥበት ሲሆን በፌዴራሉ መንግስት የማዕድን አዋጅ ቁጥር 52/1985 ዓ.ም. ውስጥ የተመለከቱትን የማዕድን ውሃንና የጂኦተርማል ክምችቶችን አይጨምርም።

WHEREAS, it is believed appropriate to efficiently organize the sector in order not only to prevent drought disaster happening on human beings, animals and nature as a whole due to persistent shortage of rain occurred in our environment but also enabling to ensure food security at family level within a short period of time and eliminate poverty; and thus as the resource is precious, it has to be given proper protection as well as conservation and economically developed to be in use and the remaining able to be transferred to the coming generation without being polluted thereof;

WHEREAS, it is found appropriate to create conducive condition in which a system of integrated water resource management is devised and implemented as well as the resource is uniformly managed in the Region, and for the facilitation of same it is proper to designate in law a responsible and supervising body that co-ordinates the work;

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Region, in accordance with the power vested in it under Article 49 sub-Article 3(1) hereby issues this proclamation.

PART ONE

General Provisions

1. Short Title

This Proclamation may be cited as "The Amhara National Regional State Water Resource Development Bureau Establishment and Determination of its Powers and Duties Proclamation No.99/2004."

2. Definition

Unless the context other wise requires, in this proclamation:

1. "Water Resource" means water on and under the surface of the earth as well as moisture in the atmosphere excluding of mineral water and geothermal deposits indicated in the Federal Government Mining Proclamation No. 52/1993.

2. "የውሃ ሃብት አስተዳደር" ማለት የውሃ ሀብት ማልማትን፣ አጠቃቀምን፣ መንከባከብን፣ መጠበቅንና መቆጣጠርን የሚመለከቱ ተግባራትን ያካተተ ነው::

3. "የውሃ ጥራት" ማለት በፊዚካል፣ በኬሚካል፣ በማይክሮ ባዮሎጂካል፣ በባክቴሮዮሎጂካል እና ራዲዮሎጂካል ገጽታው በሚታወቀው መሠረት የውሃ ጥራት መገለጫ ነው::

4. "የውሃ ሥራዎች" ማለት የውሃ ሃብትን ጠቀሜታ ላለው ተግባር ለማዋል ይቻል ዘንድ የተገነቡ ወይም የሚገነቡ ማናቸውም ሰው ሰራሽ ሥራዎች ሲሆኑ ይህም መጥለፍን፣ መገደብን፣ ማጐልበትን፣ መቆፈርን ወይም መሰርሰርን፣ መጥረግን፣ መመርመርን፣ መቆጣጠርን፣ ማጣራትን፣ መለካትን፣ ማጓጓዝን፣ ማስተላለፍን፣ ጨው አልባ ማድረግን፣ ጐርፍ መከላከያ መገንባትንና ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን የሚገልጽ ነው::

5. "ተፋሰስ" ማለት ወደ አንድ መልክዓምድራዊ አቅጣጫ የሚፈሱ የገፀ-ምድርና የከርሰ-ምድር ውሃዎች የሚያካልሉት አካባቢ ነው::

6. "የውሃ አካላት ዳርቻ" ማለት ክልሉና ወይም ርቀቱ በተቆጣጣሪውና አግባብ ባለው የመንግስት አካል አማካኝነት የሚወሰን መሬትና ማናቸውም የውሃ አካል የሚገናኝበት ሥፍራ ነው::

7. "የውሃ ተቋማት " ማለት በክልሉ ውስጥ የሚገኘውን የውሃ ሃብት በተለያዩ ዘዴዎች በማሰባሰብ፣ በማልማትና በማሠራጨት ተግባር ላይ የተሠማሩ አካላትን የሚገልፅ ነው::

2. "Water Resource Management" means activities that include Water resource development, utilization, conservation, protection and control.

3. "Water Quality" means the description of the characteristics of water defined by its physical, chemical, microbiological, bacteriological and radiological parameters.

4. "Water works" means any man made work constructed or to be constructed for the purpose of putting water to beneficial use and includes diversion, damming, developing, digging or drilling, clearing, examining, controlling, purifying, measuring, transporting, transferring, desalting dike constructing and other related works.

5. "Basin" means a geographical area described by the watershed limits of a water system including surface and underground waters flowing into a common terminus.

6. "Bank of water bodies" means land whose boundary and /or distance is determined by the supervising body and by the relevant public authority and includes any area on which water body exists.

7. "Water institutions" means to signify those bodies which are engaged in the activity of collecting, developing and distributing the water resource found in the Region by various means.

ክፍል ሁለት

ስለውሃ ሃብት ልማት ቢሮ መቋቋም፣ ተጠሪነት፣ ዓላማ፣ አወቃቀርና ስልጣን

3. ስለመቋቋም

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የውሃ ሃብት ልማት ቢሮ /ከዚህ በኋላ "ቢሮው" እየተባለ የሚጠራ/ ራሱን የቻለና ሕጋዊ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግስት አስፈፃሚ አካልና የመስተዳድር ምክር ቤቱ አባል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል::

2. የቢሮው ተጠሪነት ለክልሉ ገጠር ልማት ቢሮ ይሆናል::

4. ዓላማ

ቢሮው በዚህ አዋጅ መሰረት ከዚህ በታች የተመለከቱት አላማዎች ይኖሩታል:-

1. የክልሉን የውሃ ሃብት በመጠቀም ንፁህ የመጠጥ ውሃና የሳኒቴሽን አገልግሎት ለክልሉ ህዝብ እንዲዳረስ በማድረግ ጤናማና አምራች ዜጋን ማፍራት::

2. ከዝናብ፣ ከገፀ-ምድርም ሆነ ከከርሰ-ምድር የሚገኘውን የውሃ ሃብት በአነስተኛም ሆነ በከፍተኛ ደረጃ በማሰባሰብ፣ በማልማትና ለመስኖ፣ ለኃይል ማመንጫ፣ ለኢንዱስትሪና ለሌሎች ልዩ ልዩ አገልግሎቶች እንዲውል በማድረግ የምግብ ዋስትና የሚረጋገጥበትንና ድህነት በተፋጠነ ሁኔታ የሚጠፋበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር::

3. የከተማም ሆነ የገጠር ፍሳሾች የአካባቢ ብክለት በማያስከትሉበት ሁኔታ እንዲወገዱ በማድረግ የውሃ ሃብት አላቂ ሃብት እንደመሆኑ መጠን ያላግባብ ሳይባክንና ሳይበከል በተፋሰስና በንዑስ ተፋሰስ ደረጃ ተጠብቆ የሚቆይበትና ለትውልድ የሚተላለፍበት አስተማማኝ ሥርዓት መቀየሱንና ተገቢው መረጃ መያዙን ማረጋገጥ::

PART TWO

Establishment, Accountability, Objective, Structure and Power of Water Resources Development Bureau

3. Establishment

1. The Amhara National Regional State water Resource Development Bureau (herein after referred to as "The Bureau") is hereby established as an autonomous Regional State Executive Organ and member of the Council of Government as per this proclamation.

2. The Bureau shall be accountable to the Rural Development Bureau of the Region.

4. Objective

The Bureau shall, pursuant to this proclamation, have the objectives indicated herein under:

1. Produce healthy and productive citizens by providing clean potable water and sanitation services for the people of the Region through the exploitation of the water resource of the Region.

2. Create conducive condition for the insurance of food security and expeditious elimination of poverty by collecting and developing water resource obtained from rainfall as well as from water on and under the surface of the earth at smaller or higher level and thereby causing it to be used for irrigation, producing electricity, industry and various other services.

3. Ensure that reliable system is designed and relevant data is maintained in order that as the water resource is expendable, it has to get preserved at basin and sub-basin levels without being wasted and contaminated and thereby get same transferred to the coming generation through the making of urban as well as rural sewage disposal in a way having not caused environmental pollution.

4. ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው ባሻገር ሃብቱ ለልዩ ልዩ መዝናኛዎች አገልግሎት እንዲውል በማድረግ የዜጐችን ሕሊናዊና ባሕላዊ እሴቶች ማበልፀግ፡፡

5. ዋና መሥሪያ ቤት

የቢሮው ዋና መ/ቤት በባህርዳር ከተማ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በክልሉ ውስጥ በሌሎች ሥፍራዎች ቅርንጫፍ፣ የፕሮግራምና የፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

6. የቢሮው ስልጣንና ተግባር

ቢሮው በዚህ አዋጅ መሰረት ከዚህ በታች የተመለከቱት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የውሃ ሃብት አስተዳደርን በሚመለከት በፌዴራሉና በክልሉ መንግስታት የወጡ ሕጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፤

2. በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን ተፋሰሶችና ንዑሳን ተፋሰሶች፣ የውሃ ሃብት ክምችትና ስርጭት ያጠናል፣ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ ይይዛል፣ ይተነትናል፣ በወቅቱ ለሚመለከታቸው ያሰራጫል፣ ከሌሎች ጋር በመተባበር በሚካሄዱ ጥናቶች ላይ ይሳተፋል፣ እንዲጠኑ ያደርጋል፤

3. የክልሉ የውሃ ሃብት አስተዳደር ሁለንተናዊ አቅም በሚገባ ተገንብቶ በቅንጅት እንዲከናወን የሚመለከታቸውን አካላት ያስተባብራል፤

4. በክልሉ ውስጥ የሚገኘው የውሃ ሀብት በልዩ ልዩ የግልጋሎት አይነቶች መካከል ሚዛናዊ በሆነ መንገድ መከፋፈሉንና ጥቅም ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤

4. Prosper conscience and cultural values of the citizens by making the resource be used for the service of various recreations apart from its economic benefit.

5. Head Office

The Head of the Bureau shall be in Bahir Dar and, as deemed necessary, may establish branch, program and project coordinating Offices in other places in the Region.

6. Powers and Duties of the Bureau

The Bureau shall, pursuant to this proclamation, have the powers and duties indicated herein under:

1. Ensure and supervise that laws, regulations and directives issued by the Federal and Regional Governments concerning water resource management are observed in the Region;

2. Study basins and sub-basins, reservation of water resource and distribution found in the Region or cause same; and thereto gather, organize, maintain, analyze, and distribute data, timely to those concerned, and participate in studies conducted in co-operation with others;

3. Co-ordinate concerned bodies in order that the overall capacity of the Regional water resource management is built properly and to be executed in co-ordination thereof;

4. Supervise that the water resource in the Region is allocated in a balanced way among various types of services and employed for use;

5. የጥናትና ምርምር ፕሮጀክቶችን ጨምሮ የክልሉን የውሃ ሃብት በሚመለከት የውሃ ጉድጓዶችን ለመቆፈር፣ የተፋሰስ ልማት ሥራዎችን፣ የፍሳሽ ማስወገድ ወይም የድሬኔጅና የመስኖ እንዲሁም የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ማመንጫ ግድቦችንና ሌሎች የውሃ ሥራዎችን ለመገንባትና በጥቅም ላይ ለማዋል ጥያቄ ሲቀርብለት አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሣል፣ ይሰርዛል፤

6. የውሃ ስራዎችን በተመለከተ በራሱ አነሳሽነትም ሆነ አግባብ ካላቸው አካላት ጥያቄ ሲቀርብለት ዲዛይኖችን ይሠራል፣ እንዲሰሩ ያደርጋል፣ በመስኩ የሙያ ብቃት ማረጋገጫና በውሃ አካላት የመጠቀም ፈቃድ ይሰጣል፣ ለዚሁም ተገቢውን ክፍያ ይሰበስባል፤

7. የክልሉን የውሃ ታሪፍና የወጭ አመላለስ በተመለከተ ወጥና ፍትሃዊነት ያለው የታሪፍ የወጭ ተመላሽ አወሳሰን ሥርዓት ተቀርጾ በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ እንዲካሄዱም ያደርጋል፤

8. በክልሉ ውስጥ ለልዩ ልዩ ግልጋሎቶች ለሚውል ውሃ የተወሰነው የጥራት ደረጃ እንዲሁም ለልዩ ልዩ ፍሳሾች የተወሰነው የጤናማነት ደረጃ መጠበቁንና በስራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በፊዚካል፣ በኬሚካል፣ በባዮሎጂካል፣ በባክቴሪዮሎጂካል እና በራዲዮሎጂካል የምርመራ ዘዴዎች ተጠቅሞ ፍተሻ በማካሄድ ውሃው እንዲታከም ያደርጋል ፤

9. የሜትሮዎሎጂና የሃይድሮሎጂ መረጃዎችን ከሚመለከታቸው አካላት በመሰብሰብ፣ በመተንተንና በማሰራጨት ለልማት ሥራ እንዲውል ያደርጋል፤

10. የውሃ ሀብትን በመጠበቅ ረገድ በተለይም ክልል ዘለል የሆኑ የውሃ አካላትን በሚመለከትና በክልሉ ውስጥ በፌዴራል መሥሪያ ቤቶች አማካይነት ለሚካሄዱ ስራዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

5. Issue, renew and cancel a permit, in consultation with relevant bodies, concerning the water resource of the Region including research projects where a request submitted to it to dig water wells, construct and employ for use catchments development activities, disposal of sewage or drainage and irrigation as well as hydroelectric generating dams and other water works;

6. Make designs or cause same either in its own initiative or when a request submitted to it from relevant bodies regarding water works; and issue certificate of competence in the field as well as a permit to make use of water bodies, and collect appropriate fees from same thereof;

7. Devise and implement uniform and equitable assessment procedure for cost-return of tariffs regarding water tariff of the Region and its cost-return, and conduct studies or cause same thereon;

8. Supervise that the quality standard determined for the water used for various services as well as the standard of healthiness set for various basins is met and implemented in the Region, and when found necessary cause the water to be treated by undertaking check up through employing physical, chemical, biological, bacteriological and radiological examination mechanisms;

9. Employ meteorological and hydrological data for development activities by gathering them from relevant bodies and thereby analyzing and distributing same;

10. Provide the necessary support relating to the conservation of water resource, in particular, concerning cross Region water bodies and activities undertaken by Federal Offices in the Region;

11. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የውሃ አካላት ዳርቻዎች እንዲከለሉና እንዲጠበቁ ያደርጋል፤

12. የውሃ ሃብት አስተዳደርን የሚመለከቱ ልዩ ልዩ ክልል አቀፍ ፖሊሲዎችን /ስትራቴጂካዊ ዕቅዶችን፣ መመሪያዎችን፣ ስታንደርዶችንና ማንዋሎችን ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፤

13. የንፁህ መጠጥ ውሃ አገልግሎት ከሣኒቴሽን ሥራዎች ጋር ተቀናጅቶ እንዲካሄድ ያደርጋል፤

14. በውሃ ሃብት ዘርፍ በምርምር ስራዎች ይሣተፋል፣ የምርምር ውጤቶች በሠርቶ ማሣያ ዘዴዎች እንዲታወቁና በልማት ላይ እንዲውሉ ያበረታታል፣ የገጠሩን ሕዝብ ለማገዝ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

15. የውሃ አጠቃቀም መብቶች ይከበሩ ዘንድ በውሃ ሃብት ይዞታና አጠቃቀም ረገድ የሚነሱ ግጭቶችና ክርክሮች ፍትሃዊ በሆነ መንገድ እንዲፈቱ ያደርጋል፣ የባለመብትነት ጥያቄዎችን መርምሮ አስተዳደራዊ ውሣኔ ይሰጣል፤

16. ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የውሃ ተቋማት ደረጃውን የጠበቀ ዘላቂና ተፈላጊ አገልግሎት ይሰጡ ዘንድ ለኦፕሬሽንና ለጥገና ስራዎች ልዩ ትኩረት በመስጠት ድርጅታዊ አቅማቸው የሚጎለብትበትንና የውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት የሚጠናከሩበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤

17. በውሃ አካላት ላይ የሚደረገውን ሕገ-ወጥ የልማት እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ አስጊ የቆሻሻ ክምችት እንዳይፈፀምና የውሃ ብክለት እንዳይደርስ የፕሮጀክት ሀሣቦችን በመገምገም ተስማሚ የሆኑትን ያፀድቃል፣ የውሃ አካላት ደህንነት መጠበቁንና በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፡፡

11. Cause, in cooperation with the relevant bodies, bank of water bodies to be demarcated and protected;

12. Prepare and distribute various Region-wide policies/strategic plans, directives, standards and manuals concerning the management of water resource, and follow up the implementation of same thereto;

13. Cause clean potable water service to be undertaken being integrated with sanitation activities;

14. Participate in research works of the water resource sector, and encourage that research findings to be promoted through demonstration methods and employed for development; cause the expansion of new technologies with the view to supporting the rural people;

15. Cause conflicts and disputes arising in relation to water resource possession and exploitation to be resolved in a legitimate way in order that the rights to water exploitation are to be respected, and render administrative decision on question of ownership thereto;

16. Create conducive condition, in co-operation with bodies relevant to the matter, for the promotion of organizational capacity of water institutions and consolidation of associations of water users by providing special emphasis on operational and maintenance activities with a view to water institutions delivering continuous and required service up to their standard;

17. Follow up illegal development activities undertaken on water bodies; approve suitable project proposals through evaluation so as to protect dangerous garbage collection and water pollution, and thereby ensure the safety protection of water bodies and the proper implementation of same.

7. በተዛማጅ ድንጋጌዎች ስለ መስራት

የቢሮውን አመራር፣ የወል ስልጣን ተካፋይነትና የኃላፊዎቹን ተጠያቂነት አስመልክቶ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈፃሚ አካላትን ለማቋቋምና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 4/1988 ዓ.ም. /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 4 እና አንቀጽ 6 ድንጋጌዎችና እንዲሁም የብሔራዊ ክልላዊ መንግስቱን አስፈፃሚ አካላት እንደገና ለማደራጀትና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 60/1994 ዓ.ም. አንቀጽ 4 እና አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች ለዚህም ቢሮ በተመሣሣይ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል::

ክፍል ሦስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

8. የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

1. ከዚህ በታች የተመለከቱት ሕጎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል:-

ሀ. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 4/1988 /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 10 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 7 የሰፈሩት ድንጋጌዎች፣

ለ. የዘላቂ ግብርናና የአካባቢ ተሃድሶ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 5/1988 ዓ.ም.፣

ሐ. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈፃሚ አካላት እንደገና ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 60/1994 ዓ.ም. አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 9፣ አንቀጽ 15ና አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 5 ሥር የሠፈሩት ድንጋጌዎች::

7. Working with Related Provisions

The provisions of Article 4 and Article 6 of the Amhara National Regional State Executive Organs Establishment and Determination of their Powers and Duties Proclamation (as amended) No. 4/1995 as well as provisions of Article 4 and sub-Article 1 and 2 of Article 5 of the Reorganization of the National Regional State Executive Organs and Determination of their Powers and Duties Proclamation No. 60/2001 shall analogously be applicable to this Bureau with respect to the management, the sharing of common powers and accountability of the Heads of the Bureau.

PART THREE

Miscellaneous Provisions

8. Repealed and Inapplicable Laws

1. The laws indicated herein under are repealed by this proclamation:

A) Provisions provided under Article 10 sub-Article 1 to sub-Article 7 of the Amhara National Regional State Executive Organs Establishment and Determination of their Powers and Duties Proclamation No. 4/1995 (as amended);

B) Sustainable Agriculture and Environmental Rehabilitation Commission Establishment Proclamation No. 5/1995;

C) Provisions provided under Sub-Article 9 of Article 3, Article 15 and sub-Article 5 of Article 24 of the Reorganization of the Amhara National Regional State Executive Organs and Determination of their Powers and Duties Proclamation No. 60/2001.

2. ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

9. መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ

1. በአዋጅ ቁጥር 5/1988 ዓ.ም. የተቋቋመው የዘላቂ ግብርናና የአካባቢ ተሃድሶ ኮሚሽን መብቶችና ግዴታዎች እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 60/1994 ዓ.ም. አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 9 ና አንቀጽ 15 መሠረት የተቋቋመው የክልሉ ውሃና ማዕድን ሃብት ልማት ቢሮ ውሃን በሚመለከት ያሉት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ቢሮ ተላልፈዋል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የሰፈረው ድንጋጌ ቢኖርም የመስኖ ግንባታ ዋና ዋና ጥገናና ዕድሣት ስራዎችን በሚመለከት ለኮሚሽኑ ተሰጥተው የነበሩ መብቶችና ግዴታዎች በአዋጅ ቁጥር 15/1988 ዓ.ም. ወደተቋቋመው የውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ተላልፈዋል።

10. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1. የቢሮው አደረጃጀት በዚህ አዋጅ መሠረት ተቀርጾና በክልል መስተዳድር ምክር ቤቱ ፀድቆ በስራ ላይ እስኪውል ድረስ የውሃና ማዕድን ሃብት ልማት ቢሮ በተቋቋመበት ሕግ መሠረት ስራውን ይቀጥላል።

2. የዘላቂ ግብርናና የአካባቢ ተሃድሶ ኮሚሽን ስልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቋቋመው ቢሮ የተሰጡ ቢሆንም በአዲሱ ቢሮ ውስጥ ተገቢው አደረጃጀት እስኪፈጠርላቸው ድረስ የኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 5/1988 ዓ.ም. ተፈፃሚነቱ ለሦስት ወራት ይቀጥላል።

11. ደንብ የማውጣት ስልጣን

ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን ደንቦች የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያወጣል።

2. Any law, regulation or directive inconsistent with this proclamation shall not be applicable on matters provided in this proclamation.

9. Transfer of Rights and Duties

1. Rights and Duties of Sustainable Agriculture and Environmental Rehabilitation Commission established under Proclamation 5/1995 as well as the Rights and Duties of the Regional Water and Minerals Resource Development Bureau established pursuant to Sub-Article 9 of Article 3 and Article 15 of Proclamation No. 60/2001 relating to water are hereafter transferred to the Bureau established as per this proclamation.

2. Notwithstanding the provisions of sub-Article 1 of this Article, the Rights and Duties which were given to the Commission regarding major maintenance of construction of irrigation, and renewal works are hereafter transferred to Water Works Construction Enterprise which is established under proclamation 15/1996.

10. Transitional provisions

1. The Bureau of Water and Minerals Resource Development shall continue its duty in accordance with its establishment Proclamation pending the organizational structure of the Bureau is formulated, pursuant to this proclamation, and implemented up on approval by the Council of the Regional Government.

2. Despite that powers and duties of Sustainable Agriculture and Environmental Rehabilitation are given to the Bureau established pursuant to this proclamation, the application of the Commission's Establishment Proclamation No.5/1995 lasts for 3 months pending proper organizational structure is created in the Bureau.

11. Power to Issue Regulation

The Council of the Regional Government may issue regulations necessary for the implementation of this proclamation.

12. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ቢሮው ይህንን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሰረት የሚወጡትን ደንቦች ለማስፈፀም የሚረዱትን ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል።

13. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህርዳር
ሚያዝያ 12 ቀን 1996 ዓ.ም.

ዮሴፍ ረታ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ፕሬዚዳንት

12. Power to Issue Directive

The Bureau may issue detailed execution directives helpful for the implementation of this proclamation and regulations to be issued pursuant to this proclamation.

13. Effective Date

This proclamation shall come into force as of the date of its publication in the ***Zikre Hig Gazetta*** of the Region.

Done at Bahir Dar,
This 20th day of April, 2004

Yosef Retta
President of the Amhara
Region.